**03/30/2024** **Ref # FANA_2024_00128**

# የአቋም መግለጫ

ለዘመናት በአማራው ህዝብ ላይ በተነዛው የሃሰት ትርክት ምክንያት በሚሊዮን የሚቆጠሩ ወገኖቻችን የጥላቻ ጥቃት እና የመፈናቀል ሰለባ ሆነዋል። ከሶስት እና ከአራት ትውልድ በላይ ከኖሩባቸው እና ሃብት እና ንብረት ካፈሩባቸው ቦታዎች መጤ በመባል ተፈናቅለዋል። አማራው በህገመንግስት ሽፋን እና በመንግስት ሙሉ እገዛ ከፖለቲካ ሰልጣን ተጋሪነት እና ከኢኮኖሚ ተጠቃሚነት በስልት ተገፍቷል። ከክልሉ ውጪ በሚኖርባቸው ቦታዎች አማራው ግልጽ በሆነ መልኩ የዘር ማጽዳት ወንጀል ተፈጽሞበታል።

በተለይ የአቢይ አህመድ ኦሮሞ ተኮር መንግስት ወደስልጣን ከመጣበት ጊዜ ጀምሮ ላለፉት ስድስት አመታት ከመቼውም ጊዜ በበለጠ አማራው በይፋ በመንግስት ድጋፍ እና እውቅና በሚሊዮን የሚቆጠሩ አማራዎች ተፈናቅለዋል። በሺዎች የሚቆጠሩ አማራዎች አማራ በመሆናቸው ብቻ በአሰቃቂ ሁኔታ ተጨፍጭፈዋል። ይህ አልበቃ ብሎ ላለፉት 7 ወራት የአቢይ አህመድ ፋሺስት መንግስት በአማራው ላይ ሙሉ ጦርነት በማወጅ በአሰቃቂ ሁኔታ ንጹሃንን በከባድ መሳሪያ እና በድሮን እየጨፈጨፈ ይገኛል። በአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ሽፋን ለወታደሮቹ ሙሉ የመግደል ፈቃድ ሰጥቶ በጠራራ ጸሃይ ወጣቶችን ከቤታቸው እያወጣ በአደባባይ እየረሸነ ይገኛል። አማራው በማያወላዳ ሁኔታ የዘር ማጥፋት ታውጆበታል። መንግስት ራሱ የጀመረውን የዘር ማጥፋት ጦርነት አሳቦ እህል በማቃጠል እና እርሻ በማውደም ከፍተኛ በሆነ ፍጥነት የአማራ ክልልን ጥሪት እያወደመ ይገኛል:: ይህንን በአማራው ላይ እየደረሰ ያለውን ወደር የለሽ ጥቃት እና የዘር ማጥፋት ዘመቻ ለመመከት እና ወገኑን ለመታደግ አማራው ነፍጥ አንስቶ የማይቀለበስ የህልውና ትግል ከጀመረ ወራት ተቆጥረዋል። ለዚህ የህልውና ትግል ብዙ ጀግኖቻችን የህይወት መስዋዕትነት እየከፈሉ ሲሆን ብዙዎች የአካል ጉዳተኛ ሆነዋል።

በውጪ አገር የምንኖር የአማራ ተወላጆችም በአገር ውስጥ በወገናችን ላይ በሚደርሰው ስደት፣ እንግልት እና አረመኔያዊ ጭፍጨፋ በመቆጨት አቅማችን በቻለው መጠን የገንዘብ፣ የአድቮኬሲ እና የሞራል ድጋፍ እያደረግን ቆይተናል። ከጥቂት አመታት በፊት በአማራነት መደራጀት ባልተለመደበት ወቅት ለወገኖቻችን እናደርግ የነበረው እርዳታ በግለሰቦች እና በጥቂት የግለሰቦች ስብስብ ደረጃ የነበረ ሲሆን ካለፉት ስድስት አመታት ወዲህ ግን በተለያዩ ከተሞች እና ግዛቶች ህጋዊ የመንግስት እውቅና ያላቸው የአማራ ማህበራትን በማቋቋም የእርዳታ ማሰባሰቡን እና የአድቮኬሲ ስራውን ድርጅታዊ ሃላፊነት እና ተጠያቂነት ባለው ሁኔታ እያካሄድን ለወገናችን በፍጥነት ተደራሽ እየሆንን እንገኛለን።

ከዚህም ባለፈ በዩናይትድ ስቴትስ ኦፍ አሜሪካ ውስጥ በተለያዩ ከተሞች እና ግዛቶች የምንገኝ ስማችን ከታች የተዘረዘረው ህጋዊ እውቅና ያለን 17 ድርጅቶች በአገር አቀፍ ደረጃ ተናበን እና ተቀናጅተን ለመስራት እንዲያስችለን በፈረንጆቹ የዘመን አቆጣጠር በ2021 በፌዴሬሽን ደረጃ በመደራጀት የአማራ ማህበራት ስብስብ በሰሜን አሜሪካን (ፋና) (Federation of Amharas in North America -FANA) በማቋቋም እና ከሌሎች አጋር ድርጅቶች ጋር በመተባበር ለወገናችን ከፍተኛ እርዳታ ያደረስን ሲሆን ለዚህም በዋነኝነት የሚጠቀሱት 1) በሚሊዮኖች ብር የሚቆጠር በሁለት ዙር በቀጥታ ያደረስነው የአማራ የአደጋ ጊዜ እርዳታ (Amhara Emergency Fund) 2) እኔም ለእህቴ በሚል ስም በቀረጽነው ፕሮጀክት ከ1500 በላይ የሆኑ በወያኔ ወረራ የጾታ ጥቃት የደረሰባቸውን እህቶች ራስ ማስቻል 3) በመቶዎች የሚቆጠሩ የተሰዉ ጀግኖቻችንን ቤተሰቦች በቋሚነት መርዳትን እና 4) እስካሁን ድረስ ከታች በተዘረዘሩት የፋና ዓባል ድርጅቶች በቀጥታ እየተደረጉ ያሉ ከፍተኛ መጠን ያላቸው የገንዘብ እና የአድቮኬሲ ስራዎች በዋነኝነት የሚጠቀሱ ናቸው።

ፋና እና በስሩ ያሉ ድርጅቶች ይህንን እርዳታ ሲያሰባስቡ አንድ አማራ በሚል መርህ ከመሆኑ ባሻገር እርዳታውንም ሲያደርሱ ሚዛናዊ በሆነ ሁኔታ የችግሮችን መጠን በማወዳደር እና ለባሰባቸው አካባቢዎች ቅድሚያ በመስጠት ነው። ፋና እንደ 17 ድርጅቶች ፌዴሬሽን በአማራ አንድነት

እንዲሁም ሃላፊነት እና ተጠያቂነት ባለው ድርጅታዊ አሰራር የሚያምን ሲሆን 1) እስካሁ ፋና ያደረጋችውን እርዳታዎች እና የሰራችውን ስራዎች ከዚያም ባለፈ የፋናን አደረጃጀት እና ያለውን አቅም በስፋት ባለማስተዋወቃችን 2) መሬት ላይ አፋጣኝ እርዳታ በመፈለጉ እና እርዳታውን የሚፈልጉት ወገኖቻችን ስለፋና በቂ ግንዛቤ እና የግንኙነት መስመር ስላልነበራቸው ባለፉት ጥቂት ቀናት በተለያዩ የአማራ ክፍለሃገሮች የሚገኙ ወገኖቻችን የእርዳታ አሰባሳቢ በሚል ግለሰቦችን በኮሚቴ በማዋቀር እየወከሉ ይገኛሉ። ምንም እንኳን ይህ አካሄድ በቅን ልቦና እርዳታን በፍጥነት ለማሰባሰብ በሚል እሳቤ የተደረገ ቢሆንም ለአመታት በድርጅታዊ ሃላፊነት እና ተጠያቂነት እየሰሩ እና ወገናቸውን በከፍተኛ ጽናት እና አቅም እየደገፉ ያሉ መንግስታዊ እውቅና ያላቸው የአማራ ማህበራት ላይ የስራ እንቅፋት ከመፍጠሩ ባሻገር አልፈነው ወደመጣነው እና ልንመለስበት ወደማንፈልገው ጎጣዊ አስተሳሰብ እና አሰራር እንዳይወስደን በጽኑ እንሰጋለን። በተጨማሪም ይህ አይነቱ በግለሰቦች የሚዋቀር ኮሚቴ በህብረተሰቡ ዘንድ የሚኖረው ተቀባይነት እጠያያቂ ከመሆኑ ባሻገር የሚፈጥረው ጥርጣሬ እና አላስፈላጊ ፉክክር በውጪ የሚኖረውን አማራ ወገናችንን ግራ በማጋባት ተስፋ እንዳያስቆርጠው እና ለእርዳታ ያለውን ተነሳሽነት እንዳይቀንሰው ከፍተኛ ስጋት አለን።

ስለሆነም ይህንን ችግር በፍጥነት እና ዘለቄታዊ በሆነ መልኩ ለመፍታት እና በውጪ ያለውን ትግል ከግለሰባዊ ይዘት ወደ ድርጅታዊ ይዘት ለመመለስ ፋና በኢትዮጵያ ከሚገኙ ወገኖቻችን ጋር ቀጥተኛ ውይይት ማድረግ የጀመረ መሆኑን እያሳወቅን በዚህ በምናደርገው ጥረት ዙሪያ የአማራን አንድነት የሚደግፍ ሁሉ ትብብር ያደርግ ዘንድ አስቾኳይ ጥሪ እናቀርባለን ።

**የፋና ዓባል ድርጅቶች**

የአማራ ማህበር በሰሜን አሜሪካ (Amhara Association of America)

የአማራ ባለሙያዎች ማህበር (Amhara Professional Union)

የአማራ ማህበር በካሊፎርኒያ (Amhara Association of California, San Diego)

የአማራ ማህበር በዳላስ (Amhara People Civic Organization, Dallas)

የአማራ ማህበር በቺካጎ (Amhara Association of Chicago)

የአማራ ማህበር  በሎሳንጀለስ (Amhara Association of Los Angeles)

የሚቺጋን የአማራ ማህበር (Amhara Association of Michigan)

የአማራ ማህበር በኔቫዳ (Amhara Association of Nevada)

የአማራ ማህበር በሲያትል (Amhara Association in Seattle)

የአማራ ኅብረተሰብ ቅርስ በሚኔሶታ (Amhara Heritage Society of Minnesota)

የአማራ ማህበር በጆርጂያ (Amhara Association in Georgia)

ዋሺንግቶን እና አካባቢው የአማራ ማህበር (Washington Area Amhara Association)

የአማራ ማህበር በኮሎራዶ (Amhara Association of Colorado)

የሱ ፎልስ እና አካባቢው የአማራ ማህበር (Amhara Community in Sioux Falls, SD)

የአማራ ማህበር በኦሪገን (Amhara Association in Oregon)

የአማራ ማህበር በአሪዞና (Amhara Association in Arizona)